ቀን፡17/05/2014

# በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለውን ግድያ የሚያወግዝ ሰላማዊ ሰልፍ በሙኒክ ተካሄደ

በዳዊት መላኩ (ከጀርመን)

በጀርመን ሙኒክ ከተማ  በኢትዮጵያ ውያን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ላይ የተፈጸመውን ግድያ የሚቃወም ታላቅ ሰላማዊ ስለፍ ተካሄደ፡፡ በጀርመን ሀገር የሚገኙ በርካታ ኢትዮጵያውን  በተገኙበት የተካሄደው  ሰላማዊ ሰልፍ አላማው አንባገነኑ የወያኔ መንግስት ሰሞኑን በተላያዩ የኦሮሚያ ክልል የሚገኙ የዩኒቨርሲቲ  ተማሪዎች  ያሰሙትን ሰላማዊ ተቃውሞ አስምልክቶ ሀገሪቱን እየመራ ያለው መንግስት በተማሪወች ላይ የፈጸመውን ግድያ ፣በተለያዩ የሀገሪቱ ክልልሎች በዜጎች ላይ እየተፈጸመ ያለውን ግድያ፣ እስራት ፣መፈናቀል እና የሰባዊ መብት ጥሰት ለመቃወም ያለመ ነው፡፡ሰላማዊ ሰልፈኞቹ ያሰሙቸው ከነበሩ በርካታ መፈክሮች መካከል በተማሪዎች ላይ የተካሔደውን አረመኔያዊ ግድያ እናወግዝለን፣ ህግወጥ ማፈናቀል እና ግድያ ይቁም፣የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ፣የዞን ዘጠኝ አባላት ይፈቱ፡፡አንዱዓለም አራጌ ፣እስክንድር ነጋ ፣አቡበከር ፣በቀለ ገርባ ፣ርዕዮት አለሙ እንዲሁም ሌሎች እስረኞች ይፈቱ፡፡ነጻነት እንፈልጋለን....ወዘተ የመሳሰሉትን በጀርመን እኛ በእንግሊዘኛ በርካታ ህዝብ በተገኘበት አቅርበዋል፡፡

በካናዳ እና በአውስትራሊያ ሀገረ ስብከት ሊቀጳ ጳስ የሆኑት ብጹእ አቡነ መቃርያስ በስፍራው ተገኝተው የተለያዩ መክልቶችን ያስተላለፉ ሲሆን  ወያኔ ሀገሪቱን እያፈራረሳት በመሆኑ ሀገር ከሌለ እምነትንም ማካሄድ ስለማያቻል ህዝቡ የወያኔን ከፋፋይ ሴራ ወደ ጎን በመተው ሁሉም በጋራ በያኔ ላይ እንዲነሳ አሳስበው ልጆቻቸው ለተገደሉባቸው  ቤተሰቦች መጽናናትን ተመኝተዋል፡፡ከዚህ በታች ያለውን  ፎቶ ይመልከቱ፡፡




